MONTGOMERY COUNTY BOARD OF ELECTIONS

## የሜሪላንድ ፕሬዝዳንታዊ

# የመጀመሪያው ምርጫ (ጁን) ሰኔ 2 ነው

## ማወቅ ያለብዎት




የመራጭ መዝገብዎ በአሁኑ ስምዎ ፣ የፓርቲ ወገንተኝነትዎን እና የፖስታ አድራሻዎ እ'ንደተዘመነ ያረጋግጡ


ምርጫው የሚካሄደው በደብዳቤ ነው

ቀነ-ገደቡ፣ ግንቦት 27 ነው፥፥




የመራጭ ምዝገባ ቀነ-ገደብ ግንቦት (May) 27 ነው::





ድምጽዎን ይስጡ እና የመራጭ መሐላዎን በፊርማዎ ያረጋግጡ

ሁሉም ድምጽ ሰጪዎች አንድ በፖስታ የሚላክ የምርጫ ካርድ ያገኛሉ፥፥




የምርጫዎን ካርድ በተቻለ ፍጥነት ይላኩ:: እስከ ሰኔ(ጁን) 2 የፖስታ ማህተም ሊሰፍርበት ይገባል::

QUESTIONS? 777VOTE.ORG ★ 240-777-8500 ★ @777VOTE

**ሕይወት ያድኑ ቤትዎ ይቆዩ ከቤትዎ ይምረጡ።**

# ሞንትጎመሪ የምርጫ ቦርድ

## ስለ ሰኔ (ጁን) 2፣ 2020 ዋነኛ ምርጫ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

*(ከ ሚያዝያ (ኤፕሪል) 23 ጀምሮ አዘምን)*


ጥ1. ስለ 2020 የፕሬዝዳንታዊ ቀዳማይ ምርጫ ማወቅ የሚገባኝ ቁልፍ ነገሮች ምንድናቸው?

ጥ2. ለ2020 የፕሬዚደንት መጀመሪያ ምርጫ ቅድሚያ ድምፅ ይ ኖራልን?

ጥ3. በምርጫው ቀን በተለመደው ድምፅ መስጫ ጣቢያ በመሄድ ድምፅ መስጠት እችላለሁ?

ጥ4. የምርጫ ወረቀት መጠየቅ ይኖርብኛልን

ጥ5. የምርጫ ካርዴ የት ነው የሚላከው?

ጥ6. የምርጫ ወረቀቴን በፖስታ አድራሻዬ ባላገኝተስ?

ጥ7. የቀሪ ድምጽ መስጫ ካርድን ቀድሞውኑ ጠይቄያለሁ ። ሁለት የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን አገኛለሁን?

ጥ8. በቀሪ ድምጽ አሰጣጥ እና በፖስታ በሚላክ ድምፅ አሰጣጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ጥ9. የምርጫዬን ድምጽ ለመሙላት ምን መጠቀም አለብኝ?

ጥ10. የምርጫ ካርዴን እንዴት እመልሳለሁ?

ጥ11. የድምጽ ምርጫ ካርዴን ለመመለስ ቀነ-ገደቡ መቼ ነው?

ጥ12. የ ዩ ኤስ ፒ ኤስ ፖስታ ቤት ወይም ፖስታ መክተቻ ሳጥን የት ላገኝ እችላለሁ?

ጥ13. የድምፅ መስጫ ካርዴ ይድረሳችሁ አይደርሳችሁ እንዴት አውቃለሁ?

ጥ14. አካል ጉዳተኛ ነኝ በፖስታ ድምፅ መስጠት ያስቸግረኛል፣ ምን ሌላ አማራጮች አሉኝ?

ጥ15. የወረቀት ቅጾች ለማተምና የኢንተርኔት አገልግሎት ለሌላቸው ደምፅ ሰጪዎች ለማጋራት ተዘጋጅተዋልን?

ጥ16. አድራሻዬን ወይም የፓርቲ ወገንተኝነቴን ለመቀየር ቀነ ገድቡ መቼ ነው?

ጥ17. የምርጫ ወረቀቱን ለመጠየቅ ቀነ-ገደቡ መቼ ነው?

ጥ18. ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ንቁ ላልሆኑ መራጮች እንደማይላኩ ሰማሁ ። ለምን አይላክም? የመራጮች ምዝገባዬን እንቅስቃሴ አልባ ነው ብዬ ካሰብኩ ምን አደርጋለሁ?

ጥ19. ከዚህ በፊት በትምህርት ቤቴ አድራሻ የኮሌጅ ተማሪ በመሆኔ በቀሪ ድምጽ መራጭነት ድምጽ እሰጥ ነበር አሁን ወደ ቤቴ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ተመልሼ ብመጣስ?

ጥ20. በፖስታ በመላክ መምረጥ ለማይችሉ መራጮች የድምፅ መስጫ ማዕከሎች የት ይገኛሉ?

ጥ21. በተመሳሳይ የምርጫ ቀን ለመምረጥ መመዝገብ ይቻላልን?

ጥ22. የምርጫ ቦርድ አሰራር ከመጭበርበር ለመከላከል ምርጫ ቦርድ ምን እያደረገ ነው?

ጥ23. የምርጫ ቦርድ በይነመረብ ከጠለፋ ለመከላከል ምርጫ ቦርድ ምን እያደረገ ነው?

ጥ24. በምርጫ ቀን በምርጫ ማእከል ውስጥ ለመሥራት እንዴት መመዝገብ እችላለሁ?

ጥ25. የመራጭ ምዝገባ ካርድዬን ቅጂ እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

ጥ26. ለተጨማሪ መረጃ የት መሄድ እችላለሁ?

### ጥ1. ስለ 2020 የፕሬዝዳንታዊ ቀዳማይ ምርጫ ማወቅ የሚገባኝ ቁልፍ ነገሮች ምንድናቸው?

የሰኔ (ጁን) 2፣ 2020 ምርጫ በዋንኛነት የሚከናወነው በፖስታ ነው። ድምፅ መስጫ ወረቀቱ ቀደም ብሎ ወደ ግንበት (ሜይ) መሃል ላይ ይላክልዎታል። ሳይገኙ መምረጥ ያሚያስችሎትን ፎርም መጠየቅ አያስፈልግዎትም። ድምፅ ሰጪዎች ድምፅ መስጫ ወረቀቱን እንደተቀበሉ ወዲያውኑ ሞልተው እንዲመልሱ በጥብቅ ይበረታታሉ። እባክዎ ድምፅ የሰጡበትን ወረቀት ለመመለስ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ አይቆዩ።

ለ ህዝብ ጤና በመጠንቀቅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ ድምፅ ሰጪዎች በሙሉ የድምፅ መስጫ ወረቀታቸውን በፖስታ መልሰው እንዲልኩ ይጠይቃል። በምርጫው ቀን አራት የድምጽ መስጫ ማዕከል ይኖራል ነገር ግን እነዚህ የታሰቡት በፖስታ መላክ ለማይችሉት ብቻ ነው።

በሪፐብሊካን ወይም በዴሞክራቲክ ፓርቲ መመዝገብ ይኖርብዎታል ለወገንተኛ ቢሮ እንደ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ለሚቀርቡ የፓርቲ እጩዎች ድምፅ ለመስጠት። ግንኙነት የሌላቸው ድምፅ ሰጪዎች ለትምህርት ቦርድ ብቻ ድምፅ መስጠት ይችላሉ።

### ጥ2. ለ2020 የፕሬዚደንት መጀመሪያ ምርጫ ቅድሚያ ድምፅ ይ ኖራልን?

አይ- ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ የተነሳ ቅድሚያ ድምጽ ለ2020 ፕሬዚዳንታዊ መጀመሪያ ምርጫ ተሰርዟል። በዚህ ጊዜ፣ ለ2020 አጠቃላይ ምርጫ ቅድሚያ ድምፅ እንደሚኖር ይጠበቃል።

**ጥ3. በምርጫው ቀን በተለመደው ድምፅ መስጫ ጣቢያ በመሄድ ድምፅ መስጠት እችላለሁ?**

አይ- የሰፈር ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በአገረ ገዥው አዋጅ መሰረት የ 2020 ፕሬዚዳንታዊ መጀመሪያ ምርጫ ተዘግቷል ምክንያቱም በተለምዷ፥ዊው መሰረት የሚደረግ ድምፅ መስጠት ኖቨል ኮረናቫይረስን ሊያሰራጭ ስለሚችል በህዝብ ጤንነትና ደህነነት  ላይ ስጋት ስለሚጋረጥ ነው።

በማህበረሰቡ መካከል የ ኮቪድ 19 ቫይረስን ስርጭት ለማቀብ  እና ህይወት ለማዳን ድምፅ ለመስጠት ብቁ የሆኑ ሁሉ ድምፅ መስጫ ወረቀቱ አስቀድሞ በተከፈለ ፖስታ ይላክላቸዋል። በአካል ሄዶ ድምፅ መስጠት በጣም የተወሰነ ሲሆን ይህም በፖስታ ድምፅ መስጠት ለማይችሉ የታሰበ ነው።

**ጥ4. የምርጫ ወረቀት መጠየቅ ይኖርብኛልን?**

አይደለም። የምርጫ ካርድ መጠየቅ አያስፈልግዎትም ።

የተዘወሩ መራጮች ፣ ለጊዜው ከቤት ርቀው ያሉና ወይም የምርጫ ካርድ እስከ አርብ ግንቦት 15 ቀን 2020 ዓ፡ም፡ያልደረሳቸው የሜሪላንድ ስቴት ቦርድን ድረገጽን በመጎብኘት የመራጮች ስም መፈለጊያ መሳሪያን ወይም  በአጭር ጽሑፍ ፍተሻ CHECK ብለው  77788  ላይ  በማረጋገጥ የምርጫ ካርድ ይጠይቁ ።

**ጥ5. የምርጫ ካርዴ የት ነው የሚላከው?**

የደብዳቤ መላኪያ አድራሻዎን ለማረጋገጥ ፣ የሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ የመራጮች ስም  መፈለጊያ መሳሪያን  ወይም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት CHECK  ብለው  77788  ይላኩ ። አድራሻዎን ከቀየሩ አዲስ የምርጫ ካርድ እንልክልዎታለን ። አዲስ የድምፅ መስጫ ወረቀት በፖስታ ለመቀበል የፓርቲዎን ወገንተኝነት ወይም የደብዳቤ አድራሻዎን ለማዘመን ቀነ-ገደቡ ማክሰኞ ግንቦት(ሜይ) 26 ቀን 2020 ነው ፣ ግን ለውጥ ማድረግ ከፈለጉ እስከዚያው ድረስ አይጠብቁ ።

**ጥ6. የምርጫ ወረቀቴን በፖስታ አድራሻዬ ባላገኝተስ?**

የድምፅ መስጫ ካርድዎን እስከ አርብ ግንቦት(ሜይ) 15 ቀን 2020 ካልተ  በቀበሉ የሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ የመራጮች ስም መፈለጊያ መሳሪያን በመጎብኘት ወይም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት CHECK  ብለው  77788 ላይ ቢልኩልን እና ሊንኩን በመጫን  ተለዋጭ የምርጫ ካርድ መጠየቅ ይችላሉ ።

**ጥ7. የቀረ ድምጽ መስጫ ካርድን ቀድሞውኑ ጠይቄያለሁ ። ሁለት የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን አገኛለሁን?**

የለም። አንድ የድምፅ መስጫ ካርድ ብቻ ይቀበላሉ ።

### ጥ8. በቀሪ ድምጽ አሰጣጥ እና በፖስታ በሚላክ ድምፅ አሰጣጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ምንም ልዩነት የለም ። እ፡ኤ፡አ፡ ለሰኔ(ጁን) 2 ቀን 2020 ምርጫ የምርጫ በርድ የምርጫው ካርድ ቢጠይቁም ባይጠይቁም ለሁሉም ድምጽ ሰጪ መራጮች ይልካል ።

### ጥ9. የምርጫዬን ድምጽ ለመሙላት ምን መጠቀም አለብኝ?

ጥቁር ወይም ሰማያዊ ብዕርን እንዲጠቀሙ እንመክራለን ። እርሳስ ፣ ማቅለሚያና መቀቢያን አይጠቀሙ ።

### ጥ10. የምርጫ ካርዴን እንዴት እመልሳለሁ?

ከምርጫ ካርድዎ ጋር ስለ አሞላሉ መመሪያው ይሰጣል ። የመራጩን ቃለ መሃላ ከፈረሙ እና ቀን ከጻፉበት በኋላ በቀላሉ ፖስታ መስደጃ ሳጥን ውስጥ ሊከቱ ወይም በእነዚህ ስፍራዎች በአንዱ ሊልኩ ይችላሉ። የፖስታ ቴምብር አያስፈልግም ።

መራጮች በተቻለ ፍጥነት ድምፃቸውን እንዲመልሱ ይመከራሉ ። የድምፅ መስጫ ወረቀታቸውን ለመመለስ ቀነ-ገደብ የሚጠብቁ ሰዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አካባቢዎች የምርጫ ቦርዱ ባዘጋጃቸው የመቆለፊያ ሳጥኖች ውስጥ በአካል ቢመልሱ ከ ምርጫ ጣቢያ ረዥም ሰልፍ ሊድኑና ጊዜዎን እንዲቆጥቡ ይበረታታሉ ። እነዚህ የተመረጡ ሳጥኖችን መጠቀም የፖስታ ማህተም አያስፈልጋቸውም ።

### ጥ11. የድምጽ ምርጫ ካርዴን ለመመለስ ቀነ-ገደቡ መቼ ነው?

ድምፅ ሰጪዎች ድምጽ መስጫ ካርዳቸውን እስከ መጨረሻው ቀን ሳይጠብቁ በተቻለ መጠን በቶሎ በፖስታ እንዲልኩ ይበረታታሉ። በጊዜ መድረሱን ለማረጋገጥ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ በርድ ድምጽ ሰጪዎች የምርጫ ካርዳቸውን በ ሰኞ ግንቦት (ሜይ)25፣ 2020 እንዲመልሱ ይበረታታሉ።

የድምፅ መስጫ ካርድዎን በ ዩ. ኤስ. የፖስታ አገልግሎት የሚልኩ ከሆነ የፖስታ ቤት ማህተሙ በ ሰኔ(ጁን)2፣ 2020 ሊመታበት ይገባል።

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የፖስታ መክተቻ ሳጥኖች በአንዱ የሚልኩ ከሆነ የምርጫ ጣቢያው ከምሽቱ በ8 ፒ. ኤም ሰኔ (ጁን)2፣ 2020 ከመዘጋቱ በፊት ይከቱት ዘንድ ይገባል።

### ጥ12. የ ዩ ኤስ ፒ ኤስ ፖስታ ቤት ወይም ፖስታ መክተቻ ሳጥን የት ላገኝ እችላለሁ?

በአቅርቢያዎ ያለ የ ዩ ኤስ ፒ ኤስ ፖስታ ቤት ወይም የፖስታ መክተቻ ሳጥኖች እዚህ ያገኛሉ።

የፖስታ ቴምብር አያስፈልግም። ድምፅ ሰጪዎች በሙሉ የምርጫ ካርዶቻቸውን ሞልተው እንዲልኩ ወይም በመሰብሰቢያ ሳጥን ውስጥ በተቻለ ፍጥነት እንዲከቱ አበክረን እናበረታታለን። እባክዎን የድምፅ መስጫ ካርድዎን ለመመለስ አይዘግዩ።

ከ ዩ ኤስ ፖስታ ቤት ውጭ የምርጫ ካርዳቸውን ለመላክ የሚጠብቁ የ ምርጫ ቦርድ ድምጽ መስጫ ሳጥን በሚከተሉት ቦታዎች ከ ግንቦት (ሜይ)21 እስከ ሰኔ(ጁን) 2 (8 ፒ ኤም)ድረስ ሊጠቀሙ ይችላሉ::

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ (በአሁኑ ጊዜ 24/7 ይገኛል)18753 N. Frederick Avenue, Gaithersburg
- ሲልቨር ስፕሪንግ ሲቪክ ቢልዲንግ (በ 5/21/20 ይዘጋጃል) One Veterans Place, Silver Spring
- በ ማሪሊን ጄ ፕሬይስነር ኮሙኒቲ መዝናኛ ማዕከል (በ 5/21/20 ይዘጋጃል) 14906 Old Columbia Pike, Burtonsville
- ዊተን ቤተመጻሕፍት እና የኮሙዩኒቲ መዝናኛ ማዕከል (በ 5/21/2020 ይዘጋጃል) ፣ 11701 Georgia Avenue, Wheaton MD
- የቦህረር ፓርክ እንቅስቃሴ ማዕከል (በ 5/21/20 ይዘጋጃል) 506 South Frederick Avenue, Gaithersburg
- ጀርመንታውን ኮሙኒቲ መዝናኛ ማዕከል (በ 5/21/2020 ይዘጋጃል) 18905 Kingsview Road, Germantown
- ሮክቪል ሲቲ ሆል (በ 5/21/2020 ይዘጋጃል) 111 Maryland Avenue Rockville

### ጥ13. የድምፅ መስጫ ካርዴ ይድረሰችሁ አይደርሳችሁ እንዴት አውቃለሁ?

የሜሪላንድን ስቴት የምርጫ ቦርድ የመራጮችን ስም መፈለጊያ መሳርያ ን በመጠቀም የምርጫ ካርድዎን ሁኔታ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ፣ ወይም 77788 ላይ CHECK በማለት የቴክስት መልዕክትይላኩ።

### ጥ14. አካል ጉዳተኛ ነኝ በፖስታ ድምፅ መስጠት ያስቸግረኛል፣ ምን ሌላ አማራጮች አሉኝ?

ከቤትዎ ድምጽ መስጠት ከመረጡ፣ የ(ዌብ ዴሊቨሪ )የድር መላኪያ ምርጫ ካርድ መጠየቁ አመቺ ሊሆንልዎት ይችላል፤ በስቴት ምርጫ ቦርድ የተዘጋጀውን የኦንላይን መሳሪያ ይጠቀሙ። ድምጽዎ ላይ ምልክት ያደርጉ ዘንድ ይረዳዎታል። መሳሪያው ከተለመዱና ግለሰብ የአካል ጉዳተኞች ከሚጠቀሙባቸው ሶፍትዌሮች ጋር የተጣጣመ ነው፣ እንዲሁም የራስዎን መርጃ መሳሪያዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

በሌላ ሰው የሚረዱ ከሆነ እንዴት መምረጥ እንዳለብዎ ላይጠቁሙዎት ይችላሉ ፣ እናም አሰሪዎ ወይም የሰራተኛ ማህበርዎ መኮንን ወኪል አይሆኑም:: የእገዛ የምስክር ወረቀት በመፈረም ከምርጫዎ ካርድ ጋር በማያያዝ መመለስ ይገባቸዋል ።

የምርጫ ድምጽ ምልክት ማድረጊያ መሳርያዎች ደግሞ በምርጫው ቀን የድምፅ መስጫ ማዕከሎች ይገኛሉ የኦዲዮ ደምፅ መስጫ ማለትም ማዳመጫ ከመጻፊያ ሰሌዳ /ኪ ፓድ ጋር ፣ ጉልህ ንጽጽር ያላቸው ፊደላት መጻፊያ ማከናወኛ ሌሎችም ባህሪያትን ያካተቱና ድምፅ ሰጪዎች በግላቸውና በነጻነት ድምፃቸውን መስጠት እንዲችሉ ታቅደው ይዘጋጃሉ።

በፖስታ ድምጽ መስጠት የሚችሉ ድምጽ ሰጪዎች ሰልፉ ረጂም እንዳይሆን እንዲሁም በግንባር ድምፅ መስጠት ያለባቸውን ግለሰቦች ደህነነትና ጤንነት ለመጠበቅ በፖስታ ድምጽ በመስጠት እንዲካፈሉ ይጠየቃሉ።

**ጥ15. የወረቀት ቅጾች ለማተምና የኢንተርኔት አገልግሎት ለሌላቸው ደምፅ ሰጪዎች ለማጋራት ተዘጋጅተዋልን?**

በወረቀት ድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ማመልከቻ በሚከተሉት ቋንቋዎች ይገኛሉ፡-

እንግሊዘኛ

ስፓኒሽ

ባህላዊ ቻይንኛ

ቀለል ያለ ቻይንኛ

ኮሪያኛ

የተመዘገቡ ድምፅ ሰጪዎች የድምጽ መስጫ ፋይላቸውን ያደሱ ድምፅ ሰጪዎች እነዚህን ቅፆች በመጠቀም ድምፅ መስጫ ካርድ በፖስታ ይላካል።

በተጨማሪ በአርብ፣ ግንቦት(ሜይ) 15፣ 2020 የምርጫ ካርዳቸውን ካላገኙ፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ቅጾች መጠየቅ ይችላሉ፡-

እንግሊዘኛ

ስፓኒሽ

ድምፅ ሰጪዎች ስማቸውን ፣ የትውልድ ቀናቸውን፤ የተስተካከለ ስማቸውን ፣ የፓርቲ ወገንተኝነታቸውን እና አድራሻቸውን ያካተተ ደብዳቤ በፊርማቸው በማረጋገጥ ከምርጫ ቦርድ የምርጫ ካርድ መጠየቅ ይችላሉ።

**ጥ16. አድራሻዬን ወይም የፓርቲ ወገንተኝነቴን ለመቀየር ቀነ ገድቡ መቼ ነው?**

ድምፅ ለመስጠት የመመዝገቢያው ቀነ ገደብ ወይም የመኖሪያ አድራሻዎትን ለመቀየር ወይም የፓርቲ ወገንተኝነትዎን ለመቀየር ረቡዕ ግንቦት(ሜይ) 27፣ 2020 ነው። የድምፅ መስጠት ምዝገባዎን ለማረጋገጥ፣ የመራጮች ስም መፈለጊያ መሳሪያ ን በሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ ወይም በአጭር የፅሁፍ መልዕክትት CHECK በማለት በ 77788 ላይ ይላኩ።

**Q17. የምርጫ ወረቀቱን ለመጠየቅ ቀነ-ገደቡ መቼ ነው?**

እባክዎን የሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ የመራጮች ስም መፈለጊያ መሣሪያን በመጠቀም የመላኪያ አድራሻዎን ያረጋግጡ ወይም የመራጮች ካርድ ከመጠየቅዎ በፊት በአጭር የፅሁፍ መልዕክት CHECK በማለት በ 77788 በመላክ አድራሻዎን ያረጋግጡ ። የድምፅ መስጫ ካርድዎን እስከ አርብ ግንቦት (ሜይ)15 ቀን 2020 ካልቀበሉ በስተቀር የምርጫ መጠየቂያ ማቅረብ አያስፈልግዎትም ።

ድምጽ መስጫ ካርድ መጠየቅ ከፈለጉ የምርጫው ካርዱን በፖስታ ለመጠየቅ ቀነ-ገደቡ ማክሰኞ ግንቦት(ሜይ) 27 ቀን 2020 ነው።

የራስዎን የምርጫ ወረቀት ከቤትዎ ለማተም እና የፖስታ ቤት ኤንቨሎፕና አስፈላጊ ፖስታ ካለዎት የድር ካርድ የመጠየቂያው የመጨረሻ ቀን አርብ ግንቦት(ሜይ) 29 ቀን 2020 ነው ። የድር ማቅረቢያ ካርድ ከካውንቲው የምርጫ ቦርድ ከጠየቁ የመግቢያ እና የይለፍ ቁልፍ፣ ይደርስዎታል እንዲሁም በእራስዎ ወረቀት ላይ የራስዎን ድምጽ መስጫ በማተምና ፣ የራስዎን ፖስታ በመጠቀም ፣ ለፓስታ መላኪያም :55 ሳንቲም ይከፍሉበታል ። የድምፅ መስጫ ካርድዎ ከተመለሰ በኋላ የቦርዱ ሠራተኞች የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ከመቆጠሩ በፊት በእጅ ኦፊሴላዊ የምርጫ ወረቀት ላይ ያባዙታል ።

**ጥ18. ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ንቁ ላልሆኑ መራጮች እንደማይላኩ ሰማሁ ። ለምን አይላክም? የመራጮች ምዝገባዬን እንቅስቃሴ አልባ ነው ብዬ ካሰብኩ ምን አደርጋለሁ?**

ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለንቁ ላልሆኑ መራጮች በፖስታ አይላኩም። ምክንያቱም በሜሪላንድ ግዛት ውስጥ ሳይዘረዘሩ የተመለሱ የድምጽ ሰጪዎች በፖስታና ከሌሎች እስቴቶች መዘዋወሮ ከተገለጸን ድምጽ መስጫ ወረቀቶች አንልክም።

የመራጮች ምዝገባዎ ንቁ ላይሆን ይችላል ብለው የሚጨነቁ ከሆነ የሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ የመራጮች ስም መፈለጊያ መሳሪያን ይጎብኙ ወይንም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት CHECK 77788 በመላክ አድራሻዎን ያረጋግጡ ። እስከ አርብ ግንቦት(ሜይ) 15 ቀን 2020 ድረስ ካልደረሰዎት በስተቀር የምርጫ መጠየቂያ መሙላት አያስፈልግዎትም ። አድራሻዎን ከቀየሩ እባክዎ ወዲያውኑ አድራሻዎን ያዘምኑ ።

**ጥ19. ከዚህ በፊት በትምህርት ቤቴ አድራሻ የኮሌጅ ተማሪ በመሆኔ በቀሪ ድምጽ መራጭነት ድምጽ እሰጥ ነበር አሁን ወደ ቤቴ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ተመልሼ ብመጣስ?**

ስቴቱ የድምጽ መስጫ ካርዶችን በፋይል በሚገኘው አድራሻዎ ይላካል ። የምርጫ ቦርድ የመራጮች ሥም መፈለጊያን ወይንም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት CHECK 77788 በመፃፍ አድራሻዎን ከቀየሩ መረጃዎን በማስገባት የፖስታ አድራሻዎን ማስተካከል ይችላሉ ። ድምጽ መስጫ ካርድዎ በዚህ ግንቦት እንዲደርስዎት የሚፈልጉበትን የፖስታ አድራሻ ማዘመንዎን ያረጋግጡ ።

**ጥ20. በፖስታ በመላክ መምረጥ ለማይችሉ መራጮች የድምፅ መስጫ ማዕከሎች የት ይገኛሉ?**

እንደ ሕዝብ የጤና ልኬት ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ ሁሉም መራጮች በፖስታ የሚደርሳቸውን ድምጽ እንዲመልሱ ይጠይቃል ። በፖስታ ቤት ድምጽ መስጠት የማይችሉ መራጮች በእነዚህ ጣቢያዎች በአካል ድምጽ መስጠት የሚመርጡ ከሆነ በጣም ረጅም ተራ መጠበቅን ይጠይቃል ይህም የሌሎችን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል ።

በፖስታ ቤት በመላክ ድምጽ መስጠት የማይችሉ መራጮች በምርጫው ቀን ከእነዚህ አራት የተመረጡ አካባቢዎች ውስጥ አንዱን ለመጎብኘት በአገረ ገዢው ስለ ፊት ጭንብል ወይም ሌላ የፊት ሽፋን መጠቀምን በተመለከተ የተላለፈውን መመሪያ ማክበር ይኖርባቸዋል።

- ሲልቨር ስፕሪንግ ሲቪክ ቢልዲንግ One Veterans Place, Silver Spring
- በ ማሪሊን ጄ ፕሬይስነር ኮሙኒቲ መዝናኛ ማዕከል 14906 Old Columbia Pike, Burtonsville
- የቦህረር ፓርክ እንቅስቃሴ ማዕከል 506 South Frederick Avenue, Gaithersburg
- ጀርመንታውን ኮሙኒቲ መዝናኛ ማዕከል 18905 Kingsview Road, Germantown

መራጮች ለህዝብ ጤና እና ደህንነት ሲባል በፖስታ በመላክ እንዲመርጡ ይጠየቃሉ ። በፖስታ ቤት ድምጽ በመስጠት መምረጥ እየቻሉ በእነዚህ ጣቢያዎች በአካል ድምጽ መስጠትን የሚመርጡ ከሆነ በጣም ረጅም የተራ መጠበቅ መስመሮችን ይፈጥራሉ፥ ይህም የሌሎችን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል ።

**ጥ21. በተመሳሳይ የምርጫ ቀን ለመምረጥ መመዝገብ ይቻላልን?**

አዎ፡ ሆኖም የመራጮች ምዝገባ የጊዜ ገደብ እስከ ረቡዕ ግንቦት(ሜይ) 27 ቀን ድረስ ተራዝሟል። ስለሆነም ጥቂት መራጮች በተመሳሳይ ቀን መመዝገብና መምረጥን መጠቀም ይችላሉ ። እንደ የህዝብ ጤና ደህንነት እርምጃ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ ድምጽ መስጫ ካርድዎን በፖስታ እንዲቀበሉ እና ምርጫዎን በፖስታ መመለስ እንዲችሉ ከምርጫው ቀን በፊት እንዲመዘገቡ ይጠይቃል ።

**ጥ22. የምርጫ ቦርድ አሰራር ከመጭበርበር ለመከላከል  ምርጫ ቦርድ ምን እያደረገ ነው?**

የምርጫ ቦርድ እያንዳንዱ ምርጫ ሂደት ከመጭበርበር ለመከላከል  ለሁሉም ምርጫዎች የምናደርገውን ተመሳሳይ የመከላከያ እርምጃዎችን ይወስዳል::  በሁሉም የምርጫ ስርዓቶች እያንዳንዱ መራጭ አንድ እና አንድ ድምጽ  ብቻ መስጠቱን እንዲያረጋግጥ ተደርጎ የተቀረጸ ነው።

ማንኛውም  የማጭበርበር ክስ ማስረጃው ተመርምሮ ለፍርድ እንዲቀርብ ይደረጋል ። ማንኛውንም የተዛባ የድምጽ ማጭበርበር ከተመለከቱ ወይም ከሰሙና ካዩ ፣ የሜሪላንድ ስቴቱን አቃቤ ቢሮ  በስልክ ቁጥር 410-576-6300 ወይም በነፃ ስልክ ቁጥር  1-888-743-0023  ውስጥ ወይም መስማትና መናገር ለተሳናቸው በ 410-576- 6372  በመደወል ያሳውቁ።

**ጥ23. የምርጫ ቦርድ በይነመረብ ከጠለፋ ለመከላከል ምርጫ ቦርድ ምን እያደረገ ነው?**

የምርጫ ቦርድ ለእያንዳንዱ ምርጫ እንደሚያደርጋቸው ተመሳሳይ መሰረታዊ የሳይበር የደህንነት ጥበቃዎች ሁሉ አሁንም የጠበቀ ነው ። የስቴት ቦርድ የምርጫ ጥያቄ ማቅረቢያ እና ማከፋፈልን ጨምሮ በመላ አገሪቱ የመራጮች ምዝገባ ሥርዓትንና ደህንነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ መድቧል። የምርጫው ውጤት ከመረጋገጡ በፊት እያንዳንዱ ብቁ የሆነ መራጭ ድምጽ መስጠቱን ፣ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን መርምሮና በኦዲት አጣርቶ ከምርጫው  ፍፃሜ በኋላ ባሉት በርካታ ሳምንታት ውስጥ ሁሉም ድምፆች መቆጠሩን ያረጋግጣል።

**ጥ24. በምርጫ ቀን  በምርጫ ማእከል ውስጥ ለመሥራት እንዴት መመዝገብ እችላለሁ?**

በማህበራዊ የርቀት ሁኔታዎች ምክንያት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ ለሰኔ 2  ፕሬዝዳንታዊ ምርጫን ለማካሄድ  አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን እና ከዚህ በፊት የሰለጠኑ የምርጫ ዳኞችን ሰራተኞች ብቻ ይጠቀማል ። ለወደፊቱ ምርጫ መስራት ከፈለጉ እዚህ  መመዝገብ ይችላሉ ።

**ጥ25. የመራጭ ምዝገባ ካርድዬን ቅጂ እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?**

ለመመረጥ የመራጮች ምዝገባ ካርድ አያስፈልግዎትም ። ሆኖም ፣ ካርዱ እንዲኖርዎ  ከፈለጉ ፣ የሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ የመራጮች ስም መፈለጊያ መሣሪያን በመጠቀም ወይም የጽሑፍ መልእክት  CHECK በማለት  በ77788 ላይ መላክ ይችላሉ ።

**ጥ26.  ለተጨማሪ መረጃ የት መሄድ እችላለሁ?**

ከሰኔ(ጁን) 2 ቀን 2020 ከሜሪላንድ ስቴት የምርጫ ቦርድ መረጃ ፣ ፕሬዚዳንታዊ ቀዳማይ ምርጫ እዚህ ይገኛል ። ከቪድ-19 COVID-19 ን በተመለከተ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ መረጃ እዚህ ይገኛል ።